# ዋና የሚችል ውሃ የማይፈራ ብቻ ነው፡፡

ተኮላ መኮንን
tekolamekonen@yahoo.com

"ዝምታም ድጋፍ ነው" እንዲሉ ዝም በማለታችን የሚወራውን ሁሉ የደገፍን እንዳይመስል ፈራን፡፡ "ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም" ብለን ሰንበተን ቢሆነም ሁኔታው ግን ዝም የሚያሰኝ ሆኖ አልተገኘም፡ ለሰላም እንቁም በሚል መርህ ሰላም ለማደፍረስ የሚፈልጉ አስተያየቶችና ድምዳሜዎች ያዘሉ ጽሑፎች ማንበብ ተደጋገመ፡፡ በተለይም የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራችን የጀመሩትን "የይቅርታና የፍቅር ጎዳና" ድልድዩን ለመስበር አስፋልቱን ለማበላሸት የሚደረጉ እርብርቦሽ እያሰጉ መጡ፡፡ አገራችን እድል ሆኖ ስንቀራረብ የሚደበት ስንራራቅ የሚደሰት ሞላባት መሰለኝ፡፡ ለነገሩ ከቋሚ ይልቅ የሙትን እሬሳ የምናከብር ከሠርግ ይልቅ ቀብር የማያመልጠን በደህና ቀን ከመተባበር ይልቅ ለቀብር በተቻለን ሁሉ የምንረዳዳ ሕዝቦች ነን፡፡ በዚህ አባባል የማይስማማ ካለ በእይታው ላይ እራሱ እየዋሸ ነው፡፡

ለዛሬ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ በ aigaforum ድሕረ ገጽ ላይ "**የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ እንደሚባለው የት ይደርሳል የተባለ _"መደመር"_ የህዝብ ድጋፍና አመኔታ አጥቶ _በ4-ወራት_ መሬት ላይ ዘጭ አለ" በሚል እርእስ** የተለጠፈውን ጽሑፍ ካነበብኩ በኋላ ነው፡፡ ከአርስቱ ጀምሮ አስደነገጠኝ፡፡ ብዙ ሳላነበው መደምደሚያውን ማየት አስፈራኝ፡፡ ወይ እኔ እቶ በሸቀጥ እንዴት ያለ ሥም አለ ያለውን የቆየ ቀልድ አሰታወሰኝ፡፡ ግለሰቡ ይህንን ያለው ከማዶ ያለ ሰው ኧረ አቶ ግሞ ብሎ ሲጣራ ሰምቶ ነው፡፡ ቀልዱን እንዳለ በማቅረቤ ለቃላቱ ይቅርታ፡፡ ካለበለዚያ መልእክቱን ያጣል ብዬ ነው፡፡ ወንድሞቼ አገራችን ሰላም ይነግሥባት ይሆን? ያ ሊሆን የሚችለው በእኔ እምነት ሁላችንም ሰላምን ከፈለግን ብቻ ነው፡፡ ሁል ጊዜ "ለስርቆት" እንዲያመቸን ግርግር የምንመኝ ከሆነ ግርግሩ እኛንም እንዳያጠፋን ብንጠነቀቅ መልካም ነው፡፡ ጸሐፊው ግለሰብ ናቸው ብዬ ጀምሬ ሳነብ ቆይቼ መጨረሻው ላይ ጽሁፉ የቀረበው ከህዳሴ ኢትዮጵያ ነሓሴ 10፣ 2010 ዓ.ም. መሆኑን ስረዳ የድርጅት ጽሑፍ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ያ ታዲያ ምሬቴን ጨመረው፡፡

ለመልስ ይቀለኝ ዘንድ መልሴን ጸሐፊው ወይንም ግለሰቡ እያልኩ እመልሳለሁ፡፡ ግለሰቡ የጽሑፋቸው መግቢያ ያደረጉት በ Face book ተደረገ የሚሉትን የጠቅላይ ሚንስትራችንን ሥራ ደጋፊ ለመለየት የተደረገ ናሙና (survey) ነው ***"ለፈው ሳምንት 83% የኢትዮጵያ ህዝብ የጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አሕመድ የለውጥ ሂደት እንዳንገሸገሸው የፌስቡክ የጥናት ውጤት አረጋገጠ"*** ብለው እየተነተኑ ያቀረቡትን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የናሙናውን ሳይንሳዊነት እራሳቸውም እንደማያምኑት ያወቅሁት ደግሞ በማጠቃለያ ላይ ስለ Face book ያሉትን ካነበብኩ በኋላ ነው፡፡ እንዲህ ብለው ይደመድማሉ "ሚድያዎቻችን የጋዜጠኝነትን ስነምግባር በመጣስ ጋዜጠኞቻችን በግላዊ ስሜቶቻቸው በመገዛት ትክክለኛው መረጃ ማቅረብ ትተውታል፣ **የህዝቡ ሚድያ ፌስቡክ እየሆነ መጥቷል፡፡ ፌስቡክ ደግሞ ልክ እንደ *"መደመር"* የጨዋታ ህግ የሌለው ማንም እንደፈለገ የሚፈነጭበት በመሆኑ የብጥብጥና ዓመፅ መቀስቀሻ ሆኖ፣ በሬ ወለደ ወሬዎችና ፎቶግራፎችን በመለጠፍ ቀንደኛ የብሄር ተኮር ጥቃት ማዘዣ ሆኖዋል፡፡" ወንድሞቼ እራስን ማቃረን ማለት እንደዚህ ነው፡፡ እሳቸው ሲመስላቸው የመረጃ ምንጭ ይሆናል ካልተስማማቸው ይወገዛል ማለት ነው፡፡ ባንድ ወቅት አሜሪካ የተደረገ ናሙና ነው ተባለና "ጨው ለሰውነት ጠቃሚ መሆኑ ተረጋገጠ" ተብሎ በየጋዜጣው ላይ ተጽፎ ሲነበብ ጉድ ተባለና ለመሆኑ ጥናቱን ያስጠናውና የጥናቱን ወጭ የሸፈነው ማነው? ሲባል CAMBEL SOUP CAMPANY ነው መባሉን ስንሰማ ስቀን ነበር፡፡ ይህም የጸሐፊው ናሙና እንደዚያው ሆነብኝና ተገረምኩ ለማለት ነው፡፡ ግለሰቡ ያነሱትን በሙሉ መስመር በመስመር መተቸት ይቻላል የማይተች ነገር እጣሁበት፡፡ መተረት ትወዳለህ ካላላችሁኝ አንድ ነገር እህ ልበላችሁ፡፡** አንድ የቅኔ ተማሪ ነኝ ባይ ለእንግድነት ካረፈበት ገዳም ቅኔ ከመምህር ፊት ተቀኘና የኔታ ስህተት ካለበት አርሙኝ ቢል ያዳመጡት መምህር "አይ ልጄ ጫካ ይታረማል" አሉ ይባል ነበር፡፡ እኔም ከየት እንደምጀምር ግራ ተጋባሁ፡፡ "***የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ "*** *የሚለውን ሳነብ ጸሐፊው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይገደላሉ፤ አይሳካላቸውም ፤የታሰበው አይሆንም፤ ድልድዩም ይፈርሳል ፍቅሩም በጥላቻ ይቀየራል፤ ብለው ሊያሳምኑን እንደተነሱ ግልጽ አደረጉልኝ፡፡ በሀገራችን ለ27 ዓመት የተደረገውን የኢኮኖሚ እድገት በሰፊው ሊያሳዩን የሞከሩት ጸሐፊ ለዚያ እድገት ባመራርነት የነበሩት ዶክተር ዓብይ*

ተመሳጋኝ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን የወጤቱ ፈጣሪ መሆናቸውን ከተቀበሉ ዶክተር ዓብይ ለተሰራው ጥፋትም ተጠያቂ ነን ብለው ሲናገሩ ለምን ይከፋሉ? ከነገር ሁሉ የሚከብደው አጠፋን ማለትና ይቅርታ መጠየቅ እንጂ በጎ ሰራንማ ብሎ መኩራራት መች ከባድ ሆነ፡፡ ለምሳሌ ጥጃ ለምን እንደተመረጠ ሳስብ አካሄዱ አስፈራኝ፡የራበው ልጅ ህልሙ አንባሻ ነው የሚሉትን አይነት እንዳይሆን ብዬ፡፡

ግለሰቡ እንዳሉት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓብይ ድርጅታቸው ያመነበትን እንዲሰሩ የሰጣቸውን መመሪያ በትክክል ሥራ ላይ ያዋሉ በውሳኔ የተሰጣቸውን ሃሳብ ለሕዝብ እንደ ሰለጠነ የእቃ ነጋዴ (sales man) በትክክል መሸጥ የቻሉ ግለሰብ ናቸው፡፡ ስለሆነም በሃገራችን ታሪክ ወደር የሌለው ድጋፍ ያገኙ የደጋፊን ሳይሆን የተቃዋሚን ቡድን የማረኩ፤ ምናልባትም ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ ቅጽበት ሆድና ጀርባ የነበረውን ያገናኙ መሪ ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ስሕተት አይሠሩም ማለት አይደለም ሰው ናቸውና፡፡

አለፍ እንበልና ጸሐፊው የሚሉትን እንመልከት አብዛኛው በቅን ልቦና "እንዴ ባለፉት 27 ዓመታት በኢህአዴግ መሪነት ጨለማ ላይ ነው እንዴ የነበርነው?" የሚል በውስጡ ሲያመላልስ ነበር፡፡ ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ከእስራት የተለቀቁትን በግርፋት የተንገፈገፉትን በመአከላዊ የተሰቃዩትን ቢጠይቋቸው ጨለማው 80 ዓመት ነበር ቢሉ አይገረሙ፡፡ ለተሳሪ እንጂ ላሳሪ ጀንበር አትጠልቅምና፡ 27 ዓመት በሠራነው ልማት ውስጥ 27 ዓመት ጨለማ ነበር ማለት እውነት አይደለምን? በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን 27 ዓመት ጥፋት በመቀበል ይቅርታ የጠየቀውስ ኢሕአዴግ አይደለምን? ነጋዴዎች እስርቤት ነበራቸው ያሉት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያም ሲናገሩ በወቅቱ ምን ተሰማዎ? ይህ የድርጅቱን ድክመት አላሳየም ብለው ያምናሉን? ባለፉት ሳምንታት በስር ቤት ማቀቅን ተገረፍን፤ ጥፍራችን በጉጠት ተነቀለ፤ ብልታችን ላይ ጠርሙስ ተንጠልጠለብን፤ በሲጃራ ተተኮስን፤ ባኮርባጅ ተገረፍን፤ እያሉ በቴለቪዥን የሚመሰክሩትን ምን ሊሏቸው ይሆን? ለነዚህ ግለሰቦች እኮ ቀኑ ጨለማ ነበር፡፡ ያ ማለት መንግሥት ጥሩ ሥራ አልሠራም ማለት ደግሞ አይደለም፡፡ ኢሕአዴግ በሕዝቡ ድጋፍ የገረሰሰውና ያሽቀነጠረው የደርግ ስርዓት እኮ ጥሩ ጎን አልነበሩትም ማለት አይቻልም፡፡ በትንሹ የመሬትን ስሪት ገርስሶ ጥሏል፡፡ በዚህ ምክንያት ፊውዳሊዝምን አፈራርሷል፡ ያም ሆኖ ግን እርስዎም እንዳሉት ደርግ የገዳይ ስርዓት ነበር፡፡ ኢህአዴግ የተረከበውም

ሥልጣን ከዚህ ግፈኛ መንግሥት ነበር፡፡ ኢህአዴግ ያን ማድረጉ ግን እራሱ የጻፈውን ሕገ መንግሥት እንዲጥስ መብት አይሰጠውም፡፡ መመዘኛው ከደርግ መሻል ሳይሆን እንደመርሁ ዲሞክራት፤ የሰብአዊ መብትን መጣስ ሳይሆን የመብት አስከባሪ ሆኖ መገኘት ነበረበት ነው ክርክሩ፡፡ ዶክተር ዓብይ ተቃዋሚዎች ትክክል ነበሩ አላሉም አገራችሁ ገብታችሁ ታገሉ አሉ እንጂ፤ ክርስቲያን ሁኑ አላሉም በእምነት ሰው አይለያይም እንጂ፤ ብሔር የለም አላሉም ብሔሮች ተከባብረን ኢትዮጵያን እናጠናክር እንጂ፡፡ እኔን ተከተሉኝ አላሉም አላማና ምግባር ይኑረን እንጂ፡፡

በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ "የትግራይ ሕዝብ ወርቅ ነው" ብለው ሲናገሩ የተቆጣ አማራ፤ እኦሮሞ፤ ሲዳማ፤ ጉራጌ፤ ሱማሌ፤ ወላይታ፤ አደሬ፤ አፋር፤ ቢልሻንጉል፤ ከምባታ፤ ዶርዜ...... አላየሁም ለምን ቢባል በደረሱበት ሁሉም ወርቅ ሕዝብ እንደሆኑ መስከረዋልና፡፡ ጸሐፊው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ የተከሰቱ መፈናቀሎችን እያስታወሱን ላለፉት 3 ዓመት የነበረውን ግድያና ትንቅንቅ እንዳልነበረ ሁሉ ሳያነሱት ያልፉሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሆን ብለው ለራሳቸው ክርክር እንዲያመች ያደረጉት በመሆኑ የሌላውን ንቃተ ሕሊና እንደምክንያት እንዳመጡት ሁሉ የሳቸውን ንቃተ ሕሊናም እንድጠይቅ አደረጉኝ፡፡ በተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት በሁለት አሐዝ ያስመዘገበች አገር ከ40% በላይ ሥራ አጥነት ያላት ሃገር መሆንዋንም ይቀበሉ፡፡ እርስዎ እንዳሉት የኢኮኖሚ እድገቷን የውጭ መንግስታት ሳይቀሩ መመስከራቸው እውን እንደሆነ ሁሉ የሰባዊ መብት ጥሰት የሚካሄድባት፡ ግርፋት፤ ኢ ሰባአዊ ድርጊት የሚፈጸምባት፡ ጋዜጠኞች የሚታሰሩባት ምርጫ በትክክል የማይተገበርባት፤ አገር እንደነበረች ይጽፉ እንደ ነበር እንዴውም ሃገሪቷን ፍታዊ ሥርአት ለማስያዝ የጫና ሕግ እያረቀቁ የነበሩ መንግሥታትም እንደ ነበሩ አይርሱ፡፡ ለወንድሜ ልናገር የምወደው የእርስዎ ትልቅነት የሚለካው ለራስዎ መብት ሲቆሙ ሳይሆን ለሌሎች ጥቃት ሲቆሙ ነውና ካሉበት አጥር ውስጥ ወጥተው ባይቧርቁ እንኳን በቀዳዳው አካባቢዎን ያስተውሉ ልበልና ልደምድም፡፡ እንደ ዓብይ አይነት ሕዝብ የሚያዳምጠው መሪ እስካሁን አልነበረንም ወደፊት አይፈጠርም ግን አልልዎትም እሳቸውን እናገኛለን ብለን አላሰብንምና፡፡ ወድ ወንድም መደመር ቃሉ ካልተስማማዎት ቃሉን ትተው እንተባበር ብለው ይነሱ፡፡ እርስዎን ሳንይዝ

*ወንዙን ብንሻገር ደስተኛ እንደማንሆን ከልብ ልነግርዎ እወዳለሁ፡፡ ይህንን ሁሉ ብዬ ግን ለእርስዎ ያለኝን ክብር ልግለጽልዎ፡፡ ለምን ቢባል ምንም ውሃ ባይቋጥርም ሃሳብዎንና አመለካከትዎን አደባባይ ይዘው በመቅረብዎ ነው፡፡*

*ልቦና ይስጠን*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር*